# “በር በሩን  አሁንም አያለሁ...”

በዓሉ (አሮማይ) የት አለ

ያ ቃል ኪዳን አክባሪ

እንኳን ተልኮበት

ባስቸኳይ በጠና

አይቀርም ነበረ

ባለ ቃል ኪዳኑ

ምን መቲት ገጠመው

ይት አለ አሮማይ፤

በር በሩን ከማየት

ልመልከት ወይ ሰማይ።

በር በሩን አያለሁ ልጆቹ እንደወጡ

በመጾም በጸሎት

ደግሞ እንደ አሮማይ

በዓሉን በማክበር እነሱም እንዳይቀሩ፤

ትውልድን በመቁጠር እንዳይበላ ዱሩ።

ጋዜጠኛ ልፈፍ ሙዚቀኛም ይጨህ፤

በዓሉን ባታከክብርም ለራስህ አውጀህ

ነግ በአንተ ነውና ቀልዴ እንዳይመስልህ።

አቃጠለው አሉ ታሪክ መጽሐፉን
ድንቁርና በቀር አያውቅ ፊደልን
በዓሉን በመዋጥ ያረገዘው ምድር
ተባብሯል ያን አመጽ ጋራ ሸንተረሩም፣
ዓይኔ እንደዛገ ተመልክቶ ውስጡን
በር በሩን በማየት ቅድምም፣ አሁንም፣
ተባብሯል ያን አመጽ ጋራ ሸንተረሩም፣
ሰው ፈሪ ሆነ እንጅ ብሎ የል አልለቅም።
የዱር እሳት እኮ
ዋርካውን ሲያገየው ጭራሮም ይፈጃል፤
በዓሉን ያቃጠለው አንተንም ያቃጥላል።
ጋዜጠኛ ይልፈፍ ሙዚቀኛም ይጩህ፣
ይበል አለሁልህ፤
ለልብህ፣ ልብ አትስጥ ይተወኛል ብለህ።

© ለምለም ጺጋው፣ ለ ደራሲና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ
ባለቢታቸው ወ/ሮ አልማዝ አበራ ‘በዓሉ ይመጣል ብዬ አሁንም በር
በሩን አያለሁ’ ብለው በመለሱት፤ የተነሳሳ። (<u>በቁም ነገር መፅሔት</u> ቅፅ 13 ቁጥር 187፣
መስከረም 24/2007 የቀረበ ቃለ መጠይቅ)